

በልጆቻችን መሃል

BELIJOCHACHIN MEHAL

YOUR SUCCESS OUR MISSION



ዕለታዊ ሥራ











አቦርድ ሰብሳቢ መልዕክት

ከቡራን ጓደኞቻችን፣ ደጋፊዎቻችን፣ አጋሮቻችን፣ ወላጆች፣ መምህራን እና ተማሪዎች በሙሉ፤ በታላቅ የደስታ ስሜትና በጥልቅ የኃላፊነት መንፈስ በ«በልጆቻችን መሃል» የበጎ አድናቆት ድርጅት ስም ልባዊ ሰላምታ አቀርባለሁ። ዛሬ በዚህ መድረክ ላይ ስንቆም፣ ለትውልድ የሚተርፍ ታላቅ ሐሳብን እውን ለማድረግ የተደረገውን የጋራ ጉዞ በማሰብ ልባችን በኩራት ይሞላል።

ድርጅታችን የተመሰረተው በቀላል የዕለት ተዕለት ውይይት ሳይሆን፣ በአገራችን የትምህርት ገጽታ ላይ የተደቀነውን እጅግ አሳሳቢ ችግር በመገንዘብ ነው። በ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ውጤት ላይ የታየውና ከሚጠበቀው በጣም የወረደው አጠቃላይ ውጤት፣ በቀላሉ አንደ አንድ የተለመደ የፈተና ውጤት ሊታለፍ የሚችል አልነበረም። ይልቁንም ይህ ሁኔታ በትምህርት ስርዓታችን ላይ የተጋረጡትን ውስብስብ ፈተናዎች እና በወጣቶቻችን የዕድል በሮች ላይ ሊያስከትል የሚችለውን አደገኛ መዘዝ የሚያሳይ ጥንቃቄ የሚሻ የማንቂያ ደወል ነበር።

ይህንን አሳሳቢ ችግር በአግባቡ በመረዳትና በመፍትሔው ዙሪያ የድርሻችንን ለመወጣት በጋለ ስሜት የተነሱ በአገር ውስጥና በውጭ አገር የሚኖሩ ጥቂት የፈረንሳዩ አካባቢ ተወላጆች ተሰባሰቡ። እየንዳንዱ ወጣት ወንድም እና እህት ለመማር፣ የተደበቀ አቅሙን ሙሉ በሙሉ ለማዳበር እና ብሩህ ህይወት ለመገንባት ፍትሃዊ አድል ሊኖረው ይገባል የሚል ጽኑ እምነት አለን። ትምህርት የሰዎችን ህይወት ከመሠረቱ ለመለወጥ እና ማህበረሰቦችን ከድህነት አዙሪት ለማውጣት ከሚችሉ ታላላቅ ኃይሎች አንዱ መሆኑን በጥልቀት እንረዳለን።

የድርጅታችን ተልዕኮ ተማሪዎች ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚገቡበትን ቁጥር በላይት ማሳደግ ብቻ አይደለም። ከዚህም በላይ ተማሪዎች ከጠባቡ የመማሪያ ክፍል ባሻገር በህይወት ጎዳና ስኬታማና ፍሬያማ እንዲሆኑ ማዘጋጀት ዋናው አላማችን ነው። ወጣቶች ፈተናዎችን በብቃት እንዲያልፉ ብቻ ሳይሆን፣ ውስጣዊ ፍላጎቶቻቸውንና ተሰጥዎዎቻቸውን አውጥተው እንዲከተሉ የሚያስችላቸውን ጥልቅ አውቀት፣ የማይናወጥ በራስ መተማመን፣ አስፈላጊ የሆኑ ሀብቶችን፣ ትክክለኛ መመሪያ እና ልብን የሚያነቃቃ ሀሳቦችን እንሰጣለን።

ራዕያችን በአዲስ አበባ ከተማ በትምህርት መስክ አርአያነት ያለውና ተጠቃሽ ተቋም መሆን ነው። ማህበረሰቦች፣ በጎ ፈቃደኞች እና ቁርጠኛ ዜጎች ተሰባስበው ለወጣቶች ትርጉም ያላቸው የትምህርት አድሎችን እንዴት መፍጠር እንደሚችሉ በተግባር ማሳየት እንፈልጋለን።

የተግባር ስራችንን በዩፋ የጀመረነው በ2017 ዓ.ም. የክረምት ወራት ሲሆን፣ በመጀመሪያው ምዕራፍ 40 ተማሪዎችን በመደገፍ ነበር። በ2018 ዓ.ም. (በያዝነው ዓመት) ለተጨማሪ ተማሪዎች የክረምት የማጠናከሪያ ትምህርት አየሰጠን እንገኛለን። በቀጣይ ከክረምቱ ባሻገር የበጋ የትምህርት ፕሮግራሞችን፣ የቱቶር አገልግሎትን፣ በቴክኖሎጂ የተደገፈ ድጋፍንና ተጨማሪ የመማሪያ መርጃ መሳሪያዎችን በማቅረብ ድጋፋችንን እናጠናክራለን።

የድርጅቱ ቦርድ አንደመሆናችን መጠን፣ ኃላፊነት የተሞላበትና ብቁ መሪነት ለመስጠት፣ ድርጅቱን ከገዜ ወደ ገዜ ለማጠናከር፣ የተሟላ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ ቋሚ ቃል እንገባለን። ከዚህም በላይ በጎ ፈቃደኞቻችን፣ መምህራኖቻችን፣ ደጋፊዎቻችን፣ ወላጆች እና ተማሪዎች ለዚህ የተጋራ ታላቅ ተልዕኮ በአንድነት መቆም የሚችሉበትን ሰላማዊና ፍሬያማ አካባቢ ለመፍጠር ሁልጊዜም ከጎናችሁ እንሆናለን።

በልጆቻችን መሃል የቦርድ ሰብሳቢ

ያዕቆብ በቀለ







ለጎ ፈቃደኛ መምህራኖቻችን

















ክርሃምትን ለብርቅዬዎች

ዮሴፎ ዉባለም (ደ/ር)

የአንድ ሃገር ብርቅዬ ሀብቶቿ ተማሪዎቿ ናቸው። አነዚህ ተማሪዎች ናቸው በየዓመቱ በትምህርት ተኮትኩተው÷ በተክለ ሰውነትና በአዕምሮ አያደጉ÷ ትምህርቱ በውስጣቸው አየሰረጸ÷ ከዓመታት በኋላ በተለያየ ሙያ ተሰማርተው የሀገራችውን አምቅ ሃብት በመጠቀም ሃገራቸውንና ወገናቸውን ለማልማትና ለማገልገል የሚበቁት። ይህ ዑደት በአንከሮ ለተመለከተው አጅግ በጣም ድንቅ ነው። ብርቅዬዎቹ አነሱ ናቸው የሚባለውም ዛሬ ታዳጊ የሆኑት ተማሪዎች ነገ አብሪ ኮከብ ሆነው ትልቅ ስራ ለመስራት የሚችሉ ስለሆኑ ነው። በመሆኑም አነዚህ ብርቅዬዎች የተለየ ጥብቦ ያለው አያያዝ ይፈልጋሉ።

በተለያዩ ሃገሮች ለአነዚህ "ብርቅዬ ተማሪዎች" ትምህርት የሚሰጥበት መንገድ በተለመደው የመደበኛ መርሃ ግብሮች ብቻ አዩደለም። ይልቁንም በበጎ ፈቃደኝነት ከተለያዩ መስኮች የተሰባሰቡ ምሁራንና ታዋቂ ሰዎች ወደ ትምህርት ቤት አየተጋበዙ አውቀትና ልምዳቸውን አንዲያካፍሉ በማድረግ በተማሪዎቹ አስተሰሰብና የወደፊት አሳማ ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ ለማሳደር በሚያግዝ ስልት ይታገዛሉ። በተለይ ጀፓን በዚህ ቀመር ተማሪ ዜጎቿን በሚገባ በመቅረጽና ለሃገር ዕድገት በማዘጋጀት ትታወቃለች። በመሆኑም የረጅም ዘመን አገልግሎት ያላቸው ምሁራን በበጎ ፈቃደኝነት በአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በመገኘት ዩህንን ተግባር ያከናወናሉ።

ከላይ አንደተመለከተው ብርቅዬዎቹ ሀብቶች የሚያስተምሯቸውና አዕምሮዋቸውን የሚያንጹዋቸው መምህራኖቻችውና የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ስጪዎቹ ከፍተኛውን ሚና ይጫወታሉ። አንደሚታወቀው የመደበኛው መማር ማሰተማር ሂደት በስርዓተ ትምህርት የተደገፈና በመደበኛ መርሃ ግብር የሚመራ ሲሆን፣ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ግን ከመደበኛው ትምህርት ዩዘቱና አቀራረቡ መሰረታዊ ልዩነት ስላለው በተለየ ሁኔታ ተዘጋጅቶ ይቀርባል።

በዚህ መሰረት በ2017 ዓ.ም. የተጀመረው "በልጆቻችን መሳል" የበጎ ፈቃድ አገልግሎት፤ ከመደበኛው የመማር ማሰተማር መርሀ ግብር በተለየ መልኩና በተለየ ስልት በመከናወን አነሆ ዘንድሮም (በ2018) ተጠናቋል። በአንድ በኩል በበጎ ፈቃድ አገልገሎት የተሰማሩት በተለያዩ የትምህርት መሰኮች (በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፤ በምህንድስና በሌሎችም ሙያዎች) ተመርቀው በመስራት ላይ ያሉ፣ ወይም ሙያቸው በአነዚህ መስኮች ላይ የተመሰረተና ዝምድና ያለውና በቂ አውቀት ያላቸው ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ በተለያየ መስክ ሰፊ ልምድ ያላቸውን ባለሙያዎች በመጋበዝ አነቃቂ ንግግሮች አንዲያደርጉ ይደረጋል።

በትምህርት መስኮች ትምህርት የሚሰጥበት መንገድ ተማሪዎቹ በለመዱት ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃደኞቹ ነጻ የአቀራረብ ስልት በመሆኑ ለተማሪዎቹ አዲስ ልምድ ነው። አዲሱ ነገር ደግሞ ቀልብ ይስባል። በሌላ በኩል ደግሞ በሳምንት አንድ ጊዜ የሚመጡትም በጎ ፈቃደኞች የሚያሰተላልፉት መልእክት ልምዳችውን ያማከለና የኖሩትን÷ ተማሪዎቹ ከሚያወቁት የተለየ በመሆኑ ጾሮ ገብና አነቃቂ ነው። በመሰረቱ ከትምህርት ውጪ ብዙ ልምድ ለሌላቸው ብርቅዬዎቹ በጣም ጠቃሚና አነቃቂ ሆኖ ቀልብን በቀላሉ ይስባል። የሚተላለፈው መልእክት ተጨባጭ ሁኔታዎችን ያገናዘበ÷ በምሳሌ የተደገፈ÷ የራስንም ይሁን የሰሎችን ተሞክሮ የሚያቀርብ ሆኖ ሲገኝ አዕምሮ ከማነጹም በላይ ለተጨባጭ ተግባራት የሚያነሳሳና ትልቅ ዓላማ አንዲኖራቸው የሚያደርግ ይሆናል። በዚህ መልኩ የተላለፈ መልእክት በቀላሉ በአአምሮ ስርጾ ነገር ግን ለረጅም ጊዜ ተጽዕኖ ለያሳድር የሚችል ነው።

የሀገር ጌጦችና ብርቅዬዎችን በአግባቡ በመቅረጽ ሃገርን ለማሳደግና ለማልማት አንዲህ ዓይነት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ዕድሉች ሲፈጠሩ አጋጣሚውን በመጠቀም በጎ ፈቃደኞች ትምህርታቸውና ልምዳቸውን በማካፈል የላቀ አስተዋጽዖ ማድረግ ጥሩ ልማድ ሆኖ ሊዘወተር የሚገባውና የላቀ ጠቀሚታ ያለው ተግባር ነው። በአውነት ራሳችው በጎ ፈቃደኞቹ ተማሪዎቹ ፊት ሲቆሙና በብርቅዬዎቹ ፊት ያለውን የማዳመጥ ጉጉት ሲመለከቱ ልዩ ስሜት በሚፈጥር ሁኔታ ውስጥ ራሳቸውን ያገኙታል። በጎ ፈቃደኞቹም ደጋግመው ላራሳቸውም ሆነ ለአስተባባሪዎቹ በተጠሩ ጊዜ ሁሉ አንደሚመጡ ቃል የሚገቡበትን ሁኔታ የሚፈጥር አጋጣሚ ነው።

ብርቅዬዎቹ ብሩህ ተስፋ ፍንትው ብሎ የሚታይባቸው፤ አስተባባሪዎቹ በፍጹም ቁርጠኝነትና ኃላፊነት የሚንቀሳቀሱ÷ ከምንም በላይ ደግሞ ለተማሪዎቹ ጥልቅ ፍቅር ያላቸውና ይህንን የተቀደሰ ተግባር ለማከናወን የቆረጡ ናቸው። በመጨረሻም ይህ ዓይነቱ መርሃ ግብር መስፋፋት ስላለበት ሌሎች በየትኛውም የሃገራችን ክፍሎች የሚገኙ ወገኖች ልምድ በመቅሰም ክረምቶችን ለብርቅዬዎች አገልግሎት በመስጠት ለሃገር ለሚገኘው ትሩፋት የድርሻቸውን አንደሚወጡ ተስፋ አናደርጋለን።



የድርሻ የድርሻችንን

ወሰንሰገድ ገ/ኪዳን

የበልጅቻችን መሳል በጎ አድራጎት ድርጅት ሥራ አስኪያጅ

፩

አንዲህም ሆነ፤

በ2016 ዓም የ12ኛ ክፍል ተማሪ ተፈታኞች መሳል 5.4 በመቶ ብቻ ናቸው ያስፉት፡- አለ ትምህርት ሚኒስቴር በመግለጫው። አከለና 1 ሺህ 363 ት/ቤቶች አንድም ተማሪ ወደ ዩኒቨርስቲ አላሳለፉም አለ።

ይህ መረጀ አስደንጋጭ ነው። አሳዛኝም ነው። አሳፋሪም ነው። የሚያስቆጣም ነው፡ ፡ ትምህርት ሚኒስቴር በ2015ም አንዲህ ያለ አስደንጋጭ "ውጤት" ነግሮን ነበር። ይህንን አስደንጋጭ ዜና እኔ እና አሜሪካ የሚገኘው አብሮ አደግ ጓደኛዬ ጥሩነህ ከፍያለው (ዶ/C) በስልክ አወራንበት።

"ተማሪዎቻችን የትምህርት ሚኒስተርን ፈተና ማለፍ አልቻሉም"

"እና"

"ብንቆጣ፣ መንግስት ላይ ብንጮህ ዋጋ የለውም፤ የሚቀይረውም ነገር የለም፤ ለምን ማሕበራዊ ኃለፊነታችንን አንወጣም፤ አናም የድርሻ የድርሻችንን አናንሳ፤ ለተወሰኑ ልጆች በክረምት የሚጠናከሪያ ትምህርት አንስጣቸው።"

ይህ ሐሳብ የመጣው ከአንድ ዓመት በፊት ፈረንሳይ ለጋሲዮን የሚገኘው ሚያዝያ 23 መለስተኛ ት/ቤት ውስጥ የክረምት ማጠናከሪያ ትምህርት የሚሰጠውን የውበት በጎ አድራጎት ድርጅትን ተግባር ስለየን ነው። በ2015 ዓም እኔ በሃሳብ፣ ጥሩነህ ደግሞ በገንዘብ ድርጅቱን አግዘን ነበር።

"እኛ ይህንን ተግባር ከፍ አናድርገው፤ ጥቂት የከፍተኛ 12 ከፍተኛ ሁለተኛ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን አናግዝ፤ አንተ አዚያ ያለውን ጉዳይ አስተባብር፣ እኔ የሚያስፈልገውን የገንዘብ ወጪ እችላለሁ" አለ ጥሩነህ።

በዚሁ ተስማማን።

፪

አናም . . . በአካባቢያችን ካለውና ብዙዎቻችን ከተማርንበት ከፍተኛ 12 ሁለተኛ ደረጀ ት/ቤት ከ30 አስከ 40 ተማሪዎችን በክረምት ለማስተማር ወሰንን። ይህኑ ሀሳብ አኔ ለFacebook ወዳጆቼ አካፈልኩ። ወዲያውኑ ብዙ ቅን ሰዎች በውስጥ መስመር መጡ፡- "አናም አለን፤ የድርሻችንን አንወጣለን" አሉ። ቴዎድሮስ ከብካብ ስልክ ደወለ፤ አኔም አለሁ አለ። ለአንዲህ ያለ ሰናይ ተግባር ሁሌም ግንባር ቀደም ነው፡- ቴዎድሮስ። የፈረንሳይ ለጋሲዮን ስፖርት ክለብ ፕሬዘዳንት ነው። ሶስና ሰለሞንም በውስጥ መስመር መጣች፤ ኮምፒውተር አና ፊዚክስ አኔ አስተምራለሁ አለች። ሶስና ከኳስ ሜዳ ፈረንሳይ ለጋሲዮን ድረስ መጥታ ለማስተማር ነው የወሰነችው። የዕቆብ በቀለ አንግሊዘኛ አና ኢኮኖሚክስ አስተምራለሁ አለ። በላዩነህ ድረስ ከአዲሱ ገበያ ለፊዚክስ ትምህርት አኔም አለሁ አለ። አስራት አከበ ኢኮኖሚክስን አኔ ተወልኝ አለ። አስራት ከኮተቤ ነው የሚመጣው። መኮንን ሙሉጌታ፤ ኮምፒውተር አስተምራለሁ አለ። ሰዩድ አህመድም ኮምፒተር ለማስተማር ቃል ገባ። ሙሼ ሰሙ "በሃሳብ ከጎናችሁ ነኝ፤ በምትፈልጉኝ ቦታ አለሁ" አለን። መሰረት አራጌም ተከተለ። መሐመድ አብዱን አና ዘካርያስ ገብሩ አኔ በአካል አግኝቼ አንዲያስተምሩ ጠየቅኳቸው፤ ፈቃደኛ ሆኑ። አቤል ገ/ኪዳን አና ተገኝ በላዩም "አለን" አሉ።

በከፍተኛ 12 ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጀ ት/ቤት ታሪክ "ስትሬት A" አምጥቶ ያለፈውና ኔዘርላንድ የሚገኘው ካፒቴን ዩገዙ ጋሻው "አኔ በገንዘብ ከጎናችሁ ነኝ" አለን። በአነዚህ ሰዎች ቅንነት፤ አና ደግነት ኮራን።

፫

ከየት አንጀምር?

9ኛ ክፍል ውጤታማ ከሆኑ የደረጀ ተማሪዎች። የበለጠ ውጤታማ ሆነው አብረውን አንዲዘልቁና የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ነቅንቀው አንዲያልፉ ወጠንን። አናም በግንቦት ወር 2017 ዓም ከፍተኛ 12 ከፍተኛ 2ኛ ደረጀ ት/ቤት ሂደን "ልጆቻችን መሀል" ተገኘን። የቀድነውን ነገርናቸው። አንዲሁም አሉን፡-

"የሚያግዘን አግኝተን ነው"

አኛም ከክረምት ማጠናከሪያ ትምህርቱ ባሻገር የምገባ ፕሮግራም አንዲኖር ወሰንን። ዓለማችን የኒቨርስቲ አስኪገቡ ድረስ ውጤታማ ሆነው ከአኛ ጋር አብረው አንዲዘልቁ ነው።

፬

ለልጆቻችን የማጠናከሪያ ትምህርት የምንሰጠው ዱሮ የአፈንጉስ ጥሳሁን የግብር አዳራሽ የነበረው፣ የአሁኑ ወረዳ 2 ላዩብረሪ ውስጥ ነው። ላዩብረሪውን የያደራጀነው አኛው ነን።



በተለዩ አርቲስት አበባየሁ ታደሰ ከፍ ያለ አስተዋፅኦ አለው፦ ቤተመፅሀፋቱን በማሳደስ።

ለተማሪዎቻችን ምሳ አናቀርባለን። መጋቢ አናቶቻችን ተዘጋጅተዋል።

ዶ/ር ጥሩነህ ከፍያለው (ከአሜሪካ) አና ካፒቴን ዩገዙ ጋሻው (ከኤዘርላንድ) የምግብ፣ የኋይት ቦርድ፣ የማርከር፣ የዳስተርና ሴሎች ወጪዎችን ሸፈኑልን። (በነገራችን ላዩ ሁለቱም የፈረንሣዩ ለጋሲዮን ልጆች ናቸው)

ሐምሌ 1 ቀን 2017 ዓም፤ ለሁለት ወር የሚቆዩ የማጠናከሪያ ትምህርት መስጠት ጀመርን።





፮

የክረምቱን ሁለት ወራት በድንቅ ሁኔታ አሳለፍን። አስተማሪዎቻችን ልዩ ፍቅር ነበራቸው፦ ለልጆቻቸው። ለተማሪዎቻቸው አንዳት ዕውቀት ለማስጨበጥ የነበራቸው ትጋት ድንቅ ነበር፡ ፡ ዝናብ ሳይበግራቸው ሰዓታቸውን አክብረው የሚገኙ ድንቆች ነበሩ፦ መምህራኖቻችን።

ይህም ብቻ አይደለም፤ ተጋባዝ አነቃቂ አንግዶች ነበረን። በየሙያቸው "አንቱታን" ያተረፉ፣ አጅግ ስኬታማ ሰዎች የሕይወት ልምዳቸውን አና ተመክሮአቸውን ለማካፈል የሚሰስቱ አልነበሩም። ይህ ብቻ አይደለም፤ ለአረፍት ወደሃገራቸው የመጡ ዳያስፖራዎች አንግዶቻችን ለመሆን ዐይናቸውን አሳሹም።

ለምሳሌ ያህል ዶ/ር ጥሩነህ ከፍያለው በሃገረ አሜሪካ ሳዩንቲስት ነው፤ ባለቤቱ ወ/ሮ ዝናሽ ፍሰሃ በአሜሪካ ዎልማርት ገበያ የሒሳብ ባለሙያ ናት። በኃይሉ ፈድሉ፤ Masters in Language/Linguistics አለው። በአዳስአበባ British international School ለ20 ዓመታት አስተምሯል። በአሁኑ ወቅት ደግሞ በሀገረ ኖርዌይ Aalesund International School በማስተማር ላይ የሚገኝ ነው።



ዶ/ር አንተነህ መስፍን፤ በአማን ብሔራዊ የሳዩንስ ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ተባበሪ ፕሮፌሰር አና በአውስትራሊያ ከርቲን ከርቲን ዩኒቨርስቲ የምርምር ፊሎው ናቸው። ሚካኤል ንጉሴ ሌላው አነቃቂ አንግዳችን ነበረ። በነገራችን ላዩ Michael Negussie is a dynamic debater and civic advocate whose journey bridges continents and causes. Born in Ethiopia and raised in the U.S. after his family won a diversity visa, he discovered debate in high school as a powerful outlet for intellectual and creative expression. That passion led him to represent the U.S. at an international debate tournament—a formative experience that inspired his return to Ethiopia to launch a public debate program for high school students in Addis Ababa.

በአጭሩ የ2017 የበልጆቻችን መሀል የክረምት ማጠናከሪያ ትምህርት አነዚህን መሰል ሀገር ወዳድ ዳያስፖራ ኢትዮጵያውን የተሰተፋበት ስኬታማ ፕሮግራም ነበር።



፯

ይህ ብቻ አይደለም፤ የፌስቡክ ወዳጆቻችን ዋናዎቹ ብርታቶቻችን ነበሩ። ለምሳሌ ያህል በክረምት ትምህርት የተሻለ ውጤት ላመጡ ሶስት ተማሪዎች 20 ላያ ሺህ ብር የሚያወጣ ታብሌት የሸለሙልን የፌስቡክ ወዳጆቻችን ናቸው። አሌክስ አሸቴ የተባለ አሜሪካ የሚገኝ ወዳጃችን አጅግ ብልጫ ውጤት ላመጣው ተማሪያችን (ዮሐንስ ላለፎም) ላፕቶፕ ሸልሞልናል።

አናት ባንክ አና ጀዕፋር መፅሐፍት ደግሞ ለሁሉም ተማሪዎቻችን መፅሐፍት በስጦታ አበርክተውልናል። አናት ባንክ አና ጀዕፋር ለልጆቻችን ያበረከቱት ሸልማት 50 ላምሳ ሺህ ብር የሚያወጣ ነው።



፯

አነሆ አንዳህ አንዳህ አያለ የ2017ን የክረምት ማጠናከሪያ ትምህርት አጅግ ስኬታማ በሆነ አልኩ ነው ያጠናቀቅነው። ፕሮራማችን ስኬታማ በመሆኑም፣ ተግባራችንን ወደ በጎ አድራጎት ድርጅት ከፍ አንዳል ወሰንን። በሚያዝያ ወር 2018 ዓም ከማሕበራት ማደራጀ ሕጋዊ ዕውቅና/ፍቃድ አገኘን።

የ2018 ዓም የክረምት ማጠናከሪያ የተካሄደው "በልጆቻችን መሀል በጎ አድራጎት ድርጅት" ሥር ነው። አነሆ ትምህርቱም ሐምሌ 1 ቀን ተጀመረ። ሐምሌ 29 ቀን 2018 ዓም ተጠናቀቀ፦ በስኬት።



ጥረነህ ከፍያለው (ዶክተር)



ካፒቴን ይገዙ ጋሻው

የደጋፌዎቻችን መልዕክት

1

የአብሮ አደግ ጓደኛዬ የወሰንሰገድ ገ/ኪዳን የፌስቡክ ገፅ ተከታታዩ ነኝ። እጅግ ጠቃሚ ጉዳዮችን የሚዳስሰው ገፁ፣ አንድ ቀን ትኩረቴን በጣም የሳበ አቅርቦ አየሁ። ዩህ ዘገባ በፈረንሳዩ ሰጋሲዮን አካባቢ በውበት በጎ አድራጎት ድርጅት ደጋፊነት ለረዥም ጊዜ በአንድ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት የክረምት ማበረታቻ ትምህርት አንደሚሰጥ የሚያወሳ ነበር። ከዚህ ዘገባ በጓሳ ወሰን እና አኔ በስልክ ዩህንን ተግባር የምንደግፍበት፣ ወዩም በሌላ አካባቢ የምናባዛበትን መንገድ ተወያየን። ለአንድ ዓምትም ውበት በጎ አድራጎት ድርጅትን ደገፍን።

ዩህ ከሆነ ከጥቂት ወራት በጓሳ ትምህርት ሚኒስቴር ለሕዝብ አስደንጋጭ ዕውነታን ያዘለ መረጃ አሰራጨ። ዩህም በሀገሪቱ ካሉ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በሸህ የሚቆጠሩት አንድም ተማሪ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አለማሳለፋቸውን የሚያትት ነበር። ዜናው ልብ ሰባሪ ነበር። አኔ ራሴ የመንግስት ት/ቤት ውጤት አንደመሆኔ፣ የዚህ የትምህርት ጥራት ጉድለት ተጋላጮች አነማን አንደሆኑ መገመት የሚያዳግት አልነበረም።

ከዚህ በጓሳ ነበር ወሰን፣ ያዕቆብ በቀለ አና አኔ ባለን አቅም፣ ባደግንበት አካባቢ ያሉትን የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ለመደገፍ የተነሳሳነው። ሀሳባችን ችግሩን ሙሉ በሙሉ መፍናተት ሳይሆን፣ ጥቂት ተማሪዎችን በተቻለን መጠን በዕውቀት በማገዝ ለሌሎችም ምሣሌ የመሆን ተስፋ ነበር የሰነቅነው። ለዚህም አኔ ካለሁበት ሆኜ በሃሳብ አና በዋነኛነት በገንዘብ ለመደገፍ ወሰንኩ። ወሰን አና ያዕቆብ ደግሞ መሬት ሳይ ያለውን ሥራ ለማከናወን ተጉ። ዩህም ተግባር ሁለት ዓመት ሆነው።

በአነዚህ ሁለት ዓመታት እጅግ ልብ የሚያሞቁ ተግባራትን አዩተናል። በተለይም የተማሪዎች የትምህርት ጥማት፣ የበጎ ቃድ መምህራኖች ፍፁም ልባዊ አገልግሎትና ቁርጠኝነት ድንቅ ነበር። ትምህርት ዘርፈ ብዙ ተግዳሮታችንን አሸንፈን፣ ነገ ወደተሻለ የኑሮ ዘዩቤ የምንፌገርበት ዋነኛ አና ፈጣኑ መንገድ ነው። ዩህንን ሽግር ዕውን የሚያደርጉትን የዛሬዎቹን ተማሪዎች ለማብቃት ሁላችንም አንትጋ።

ጥረነህ ከፍያለው (ዶክተር)

ከአሜሪካ

2

አኔ የተወለድኩትና ያደግኩት በትግር አና በዘቅተኛ ገቢ በሚኖር ቤተሰብ አዘሁ ፈረንሳዩ ሰጋሲዮን 11 ቀበሌ ውስጥ ነው። የድህነትን ፈተና፣ የቁሳቁስ አጥረትን አና የወደፊት ተስፋን አጥር አድርጎ የመጋረጡን ስሜት በቅርበት አውቀዋለሁ። ነገር ግን በነዘህ ሁሉ ተጽዕኖዎች ውስጥ ሆኜ፣ ትምህርት የህይወቴን አቅጣጫ የመቀየር ትልቁ ቁልፍ መሆኑን ተረዳሁ፤ በብርታትና በትጋት በመማሬም ዛሬ ለደረስኩበት የስኬት ደረጃ በቅቻለሁ።

ወንድሜ ወሰንሰገድ ዩህንን ተጨማሪ የክረምት ማጠናከሪያ የትምህርት ድጋፍ (ቱቶሪያል) ለማዘጋጀት ማሰቡንና የኛን የሰፈሩን ሰው ድጋፍ አንደሚያስፈልግ ሲነግረኝ በደስታ ነበር የተስማማሁት። ምክንያቱም ከራሴ ያለፈ ህይወት በመነሳት ነው፤ ድህነት ጊዜያዊ ፈተና አንጂ የተማሪዎችን ህልም አና አቅም ማቀም የሚችል አንቅፋት መሆን አንደሌለበት ሙሉ በሙሉ ስለምታመን ነው።

ውድ ተማሪዎች! ዛሬ የምታልፉበት አስቸጋሪ የኑሮ ሁኔታ የወደፊት አጣ ፈንታችሁን የመወሰን አቅም የለውም። ድህነት የህይወታችሁ ጊዜያዊ ምዕራፍ አንጂ የመጨረሻ መዳረሻችሁ አይደለም። በአጀችሁ ያለው ትልቁና ማንም ሊቀማችሁ የማይችለው መሳሪያ የአውቀት ጥማታችሁ አና የውስጥ ጽናታችሁ ነው። አነዚህ የተዘጋጁላችሁ ተጨማሪ የትምህርት ድጋፎች ከአኖ የቀረቡ የፍቀር፣ የድጋፍ አና የተስፋ አጀት ናቸው፤ አናንተ ደግሞ ዩህንን አድል በአግባቡ በመጠቀም፣ ሌሊትና ቀን በትጋት በማንበብ ለሳቀ ስኬት መብቃት አለባችሁ። ህልማችሁ ከምትኖሩበት ወቅታዊ ሁኔታ በላይ አጅግ ትልቅ አንደሆነ ሁልጊዜ አመኑ።

አኔና ሌሎቹም ወንድም አህቶቼ ዩህን የተቀደሰ ስራ ድጋፍ የምናደርገው፣ በውስጣችሁ ያለውን ትልቅ አቅም ስለምናውቅ አና ነገ አናንተም ስኬታማ ሆናችሁ ለሌሎች ወገኖቻችሁ መብራት አንደምትሆኑ ስለምንተማመን ነው። ትምህርታችሁን በልየ ትኩረት ተከታተሉ፣ መሰናክሎችን ወደ ጥንካሬ ለውጡ፣ አናም ወደ ታላቅነት የሚወስደውን መንገድ በጥንካሬ ተጓዙ። የአናንተ ስኬት የራሳችሁ ድል ብቻ ሳይሆን የቤተሰቦቻችሁ ኩራት አና የሀገራችን ተስፋ ነው!

ካፕቴን ዩገዙ ጋሻው

2017 አርአያዎቻችን





የክረምት ትምህርት ስንጀምር፣ ጥቂት ሰዎች ልምዳቸውን ቢያካፍሉን ብለን ነበር ያሰብነው። ነገር ግን ከአቀድነው፣ ከገመትነው በላይ ሆነ። ከአሜሪካ፣ ከኖርዌይ፣ ከኡጣን ወዘተ ለአረፋት የመጡ 5 ወገኖቻችን ከእኛ ጎን ነበሩ። ያውም በእነሱ ፕሮግራም ሳይሆን፣ በእኛ ፕሮግራም ለልጆቻችን ዕውቀታቸውን አካፍለዋል። በአጠቃላይ 19 ሰዎች ከዕውቀታቸው ከፍለው ሰጥተውናል፤ ተመክሮአቸውን አካፍለውናል። መክረውናል፤ ዘክረውናል። አርአያ ሆነውናል።





እነሆኝ አርአያዎቻችን፦

(1) ብርቱካን ሚደቅሳ

(2) ሙሼ ሰሙ

(3) ዶ/ር ጥሩነህ ከፍያለው ፤

(4) ዝናሽ ፍሰሃ

(5) በኃይሉ ፈድሉ ፣

(6) ቴዎድሮስ ክብካብ

(7) ተስፋዬ ኃ/ማርያም፤

(8) ረ/ፕ/ር ነብየ ባዬ

(9) ሰርፀ ፍሬስብሃት

(10) ሚካኤል ንጉሴ

(11) ዶ/ር ሐውለት አህመድ፣

(12) ዶ/ር ኤርሲዶ ለንደቦ፣

(13) አቶ ብሴን አጥናፉ

(14) ደራሲ ውዳባት ገዳሙ ፣

(15) ዶ/ር አንተነህ መስፍን፣

(16) ሠናይት ጥበቡ፣

(17) ኢያሱ በሬንቶ በኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርስቲ የፍልስፍና መምህር እና ተመራማሪ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሶስተኛ ዲግሪ ተማሪ፣ በትምህርት እና በማህበራዊ ጉዳይ ተመራማሪ፣ አሰልጣኝ እና አማካሪ፤

(18) ኢንጅነር ጌታሁን ሐራሞ እና

(19) ዲያቆን፣ ዶክተር/ ፓዩለት ናትናኤል ስንታየሁ ናቸው።

















2018











የክረምት ማጠናከሪያ ትምህርት ከጀመርን አንስቶ፣ አነቃቂ ንግግር የሚያደርጉ ታላላቅ ሰዎችን አንጋብዛለን። በ2018 ዓም ዘወትር አርብ፣ አርብ የአነዚህ አንግዶች ቀን ነው። ልጆቻችን ዕድለኞች ናቸው፤ ከታላላቅ ሰዎች አግር ስር ቁጭ ብለው ተመክሮአቸውን ይካፈላሉ።

ለምሳሌ ዶ/ር ዮሴፍ ውባለም፣ በትምህርት ዘርፍ የወጣላቸው ባለሙያ (አማካሪ) ናቸው። ዶ/ር አሉላ ፓንክረስት በማሕበራዊ ጥናት ዘርፍ "አንቱ" የተባሉ ምሁር ናቸው። ፀጋሥላሴ ስለሺ (ዶ/ር) ሀገረ አሜሪካ ነዋሪ ነው፤ ኢኮኖሚስት ነው። በአሜሪካ የአንድ መንግስታዊ መ/ቤት አማካሪ ነው። ሀለተኛ ደረጀ ትምህርቱን የተማረበት መጥቶ ስኬቱን ሲናገር ልጆቻችን ገፅ ላይ የታየው መደነቅ ልየ ነበር።

አንድ ሺህ ስኬታማ የልብ ቀዶ ሕክምና ያካሄደው ዶ/ር ፈቃደ አግዋር ተመክሮ ለልጆቻችን አስደናቂ ነበር። የሶፍትዌር ኢንጅነሩ ብርሃን ነጋ የሕይወት መንገድ አጅን በአፍ ያስጫነ ሆነ ነው ያሰፈው። ሰርፀ ፍሬስብሀት፣ የሕይወት መንገዱን ልምዱን በጥበባዊ መንገድ (አሱም የተማረበት ት/ቤት መጥቶ ነው) ሲያቀርብ ልጆቻችን ትንፋሽ አልነበራቸውም።

ሐውለት አሕመድ (ዶ/ር) ልክ አንደአምናው በጥዑም ስልት ነበር የሁልጊዜ ስንቅ የሚሆን ትምህርት የሰጠቻቸው። የ26 ዓመቱ የደብረብርሃን ዩኒቨርስቲ የሕግ መምህር የሆነው በላይ አሸናፊ የ"ይቻላል" መንፈስ ነበር ያሰረፀባቸው። ሚካኤል ጥላሁን፤ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በተፈጥሮ አና ምዘና ሳይንስ የስነ ምድር ትምህርት ክፍል ባልደረባና ሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ የከርሰ ምድር ውሃ ባለሙያ ነው። የሀገርን ሀብት በአግባቡ ስለመጠቀም፣ በሀገር ስለመኩራት....ወዘተ የነገራቸውን የሰሙት በምሰጢ ነበር።

ለዚህ ነው ልጆቻችን ዕድለኞች ናቸው የምንለው። አናም ...አነዚህ የ2018 ዓም አርአያዎቻችንን አናመሰግን ዘንድ ግድ ነው።

ደግመን ደጋግመን አናመሰግናለን !!